# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 15 ነሐሴ 22 2000 ዓ.ም


## ባለስልጣናትና ኢንቨስተሮች ሀብታቸውን እያሸሹ ነው።

## የኑሮ ውድነቱ ጥቂቶችን አበለጸገ፣አብዛኛውን አቆረቆዘ

በኢትዮጵያ የተፈጠረውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተከትሎ የመንግሰት ባለስልጣናትና ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን በውጭ ባንኮች እያሸሹ እንደሚገኙ ምንጮቻችን ገለጹ።ለመንግስት ገንዘብ በማበደር የሚታወቀው የአለም ባንክ ሳይቀር፣ የአለም ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተስፋ መቁረጡን እየተናገረ ባለበት ወቅት የመንግስት ባለስልጣናት ና አንዳንድ ኢንቨስተሮች፣ በአገሪቱ ሊፈጠር የሚችለውን ቀውስ በመፍራት ገንዘባቸውን ማሸሽ ጀምረዋል። አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የመንግሰት ተቀጣሪ የሆኑ ግለሰብ እንደተናገሩት የውጭ ምንዛሬ መመናመንና የብር ዋጋ መውደቅ አገሪቱን በከፋ ችግር ውስጥ ይጥላታል ተብሎ በመታመኑ፣አንዳንድ ባለስልጣናት ካለፉት ሶስት ወራት ጀምሮ ገንዘብ በከፍተኛ መጠን ወደ ውጭ አገራት እያሸሹ ነው። ባለስልጣኖቹ የንግድ ድርጅቶችን በስውር በማንቀሳቀስ የሚታወቁ ሲሆኑ፣ ከተለያዩ ድርጅቶቻቸው የሚሰበስቡትን ገንዘብ በፍጥነት ወደ ውጭ አገራት በማስወጣት ላይ ናቸው፤ አብዛኛው ገንዘብ የሚሄደውም ለንደን ወዳሉ ባንኮች እንደሆነ ግለሰቡ ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡም ሆነ ኢንቨስት አድርገው እቃ ለማስገባት የሚፈልጉ ሰዎች የውጭ ምንዛሬ በመጥፋቱ ምክንያት ሲጉላሉ መታየት የተለመደ ነው።ከተወሰኑ ወራቶች በፊት እቃ ለማስገባት ኤል ሲ የሚከፈት ሲሆን፣ኤል ሲ ለመክፈትም እስከሶስት ወራት መጠበቅ ግድ ይል ነበር፣ሰሞኑን ግን እስከናካቴው የውጭ ምንዛሬ የለም በመባሉ ባለሀብቶች ተደናግጠዋል።

የኢህአዴግ ባለስልጣናት ያለችውን የውጭ ምንዛሬ በመቀራመት፣ገንዘባቸውን በማሸሽ ላይ መሆናቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው ያሉት ባለስልጣኑ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዝም ብሎ መመልከት እንደሌለበት ተናግረዋል።አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የታየው የውጭ ምንዛሬ እጥረት በብዙ ምክንያቶች ሊፈጠር እንደሚችል ባለሙያዎች ይናገራሉ።እንደ አለም ባንክ ባለስልጣናት ደግሞ ችግሩ በተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት የመጣ ሲሆን የወያኔ መንግስት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት አስመዘግባለሁ በሚል ምክንያት፣ እውነታውን ግምት ውስጥ ያላስገባ ወጪ በማውጣቱ አሁን ለተፈጠረው ችግር መንስኤ ሆኗል ተብሏል።

በኢትየጵያ የተከሰተው የውጭ ምንዛሬ እጥረት በአጠቃላይ እቃዎች ላይ የዋጋ ንረትን ሲያስከትል፣ የተፈጠረውን የዋጋ ጭማሬ ለማረጋጋት ወይም የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ለመጨመር ምንም ጥረት ባለመደረጉ ህዝቡ ለስቃይ ተዳርጓል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ሰዎች እንደሚገልጹት የኑሮ ውድነቱ ከሚሸከሙት በላይ ሆኖባቸዋል። አብዛኛው ህዝብ የግብርናና የፋብሪካ ምርቶችን ገዝቶ ለመጠቀም እየተቸገረ ነው። የአገዛዙ ባለስልጣናት ለሰራተኛው ደሞዝ እንጨምርልሀለን እያሉ ሰራተኛውን ለማባበል ጥረት ቢያደርጉም፣ ደሞዝ መጨመር የገንዘብ ግሽበትን ከማባባስ ውጭ ሌላ መፍትሄ እንደማያመጣ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በተፈጠረው የኑሮ ውድነት በመጠቀም ፣ጥቂት የህወሀት ድርጅቶችና ባለስልጣን ኢንቨስተሮች ሀብት እያካበቱ እንደሚገኙ ምንጮቻችን አክለው ይናገራሉ።ብዙ ባለስልጣኖች ከሁለት ያላነሱ ቤቶችን በመገንባት ላይ ሲሆኑ፣ አንዳንዶች ደግሞ በእጅ አዙር በውጭ አገር የንግድ ተቋማትን ከፍተው በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ብዙዎቹ የህወሀት ባለስልጣናት ከግለሰብ ነጋዴዎች ጋር እየተሻረኩ ንግድ እንደሚያካሂዱ የውስጥ ምንጮች አክለው ይገልጻሉ።

ግዜ

## ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ፤በጂቡቲ ወደብ ንብረቷን መወረስ ጀመረች

ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ብድር ለሐረር መጠጥ ውሀ ማስፋፊያ ተብሎ የተገዛ የቧንቧ ቁሣቁስ በጂቡቲ ወደብ ተወረሰ።በብድር በተገኘ ገንዘብ፤ በውሀ ሀብት ሚኒስቴር ተቆጣጣሪነት የተገዛው ንብረት የተወረሰው፤ ዕቃውን ገዝቶ ለማስገባት ጨረታ አሸንፏል የተባለውና “ዋት ኢንተርናሽናል”ተብሎ የሚጠራው የአገር ውስጥ ኩባንያ የኪራይ ዋጋ ሳይከፍል ዕቃውን ለረዥም ጊዜ በወደቡ መጋዘን አስቀምጧል በሚል ምክንያት ነው።

ነገሩን ዕንቆቅልሽ ያደረገው፤ ዕቃውን ለመግዛትና ሐረር ከተማ ድረስ ለማድረስ ጨረታውን አሸንፏል የተባለውና የወደብ ኪራይ አልከፈለም የተባለው “ዋት”የተሰኘ ኩባንያ ፤በህዝብ ስም በብድር ከተገኘው ገንዘብ፤ በቅድሚያ ክፍያ መልክ 28 ሚሊዮን ብር መውሰዱ ነው።የወደቡ አስተዳዳሪ ዱባይ ፖርት ኢንተርናሽናልም፤ የኢትዮጵያው ኩባንያ ዕቃውን ገዝቶ ለረዥም ጊዜ በመጋዘን በማስቀመጡ የኪራዩ ዋጋ ከፍ እያለ መጥቷል በሚል ምክንያት ዕቃውን አውጥቶ ለነጋዴዎች ሸጦታል።

ሥር የሰደደው የሐረር ከተማ የመጠጥ ውሀ ችግር ዘወትር በሙሰኞች ምክንያት ሊፈታ አለመቻሉ ያሳዘናቸውና ያስቆጣቸው አካላት፤ “ የዓሣ ግማቱ ከአናቱ ነው። ለሙሰኞች እንደ አሸን መፍላት ዋነኛ ምክንያት የሆነው የመለስ አገዛዝ የቡድነኝነት መዋቅር ፣፣ወደ ገጽ2 ዞሯል፣

## አማረና- እሥራቱ

ትናንት በዋስ ሳይፈታ እንዳልቀረ በተገመተው በአማረ አረጋዊ እስራት የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው።የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት የሆነው አማረ፤ ህወሀት አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፤ቀጥሎም የዜና አገልግሎት ሀላፊ ሆኖ የሠራ ሲሆን፣ ሥራውን ከለቀቀ በሁዋላ ደግሞ የራሱን ድርጅት በማቋቋም ሪፖርተር የተባለውን ጋዜጣ በማሳተም ላይ ይገኛል።ሪፖርተርና አማረ፣ በህወሀት ደጋፊነታቸው የሚታወቁ ሲሆን፣ወትሮ ሚዛናዊ ነው የተባለለት ሪፖርተር ፤ በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ጊዜ ከፍተኛ መዋዠቅ በማሳየቱ ተዓማኒነቱ ጥያቄ ውስጥ ፣፣ወደ ገጽ2 ዞሯል፣

## የግንቦት 7 ንቅናቄ አጭር ሞገድ ሬድዮ ስርጭት

## መስከረም 1፣ 2001 ዓም ይጀመራል

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም መስከረም 1 ቀን 2001 ዓ.ም ሐሙስ ምሽት ይጀምራል።

የህዝብ ግንኙነት ክፍል

# ርእሰ አንቀጽ

# ዳግም የሬሳ ንግድ!

## «ጥሬ ገንዘብ ካልሆነ የምግብ እርዳታ አልቀበለም» መለስ ዜናዊ

«የምግብ ዕጥረት እንጂ ረሃብ ፈፅሞ የለም፣ በሚገባ ያልተመገቡ ህጻናት እንጂ የተራቡ ህጻናት የሉም» መለስና ባልደረቦቹ በሃራችን ላይ በአደባባይ ለመንገሱ ጥናት የማያስፈልገውን ረሃብ ለመካድ የሚጠቀሙበት የሰሞኑ የቋንቋ ጅምናስቲክ ነው:: ከጥቂት ወራት በፊት ረሃብ መግባቱን በማስረጃ ያቀረቡ የአልጀዚራና የበቢሲ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ቴሌቪዝን በተዘጋጀ የአንድ ሰአት ፕሮግራም፣ «የጋዜጠኛነት ስነምግባርና ሞራል የሌላቸው» መሆናቸውን እየተጠቀሰ፣ ረሃብ በሌለበት ረሃብ ገብቷል ብለው ዜና ሰሩ ተብለው፣ ሲወገዙ አገሬው «ይሉሽን አልሰማሽ» እያለ ፕሮግራሙን በትዝብት እንደተ ከታተለ እናስታውሳለን:: ይሁንና የረሃብን ነገር መለስ ካደውም፣ ሌላም ማሳመሪያ ስም ሰጠው፣ ረሃብ ዛሬ በኢትዮጵያችን አይኑን አፍጦ ጥርሱን አግጦ የቆመ ጋሀድ ሆኗል:: የሁኔታው አስከፊነት ያሳሰባቸውና መለስን ላለማስቀየም የረሃብ ጉዳይ ማንሳት አቁመው የነበሩ የውጭ የዜና አውታሮች፣ የየመንግስታቸው ቡራኬ ታክሎበት ይመስላል በቅርቡ በቀን 400 ሰዎች በደቡብ ብቻ እየሞቱ እንደሆነ ዘግበዋል ::

በቆሎ ለነዳጅ ዘይት የሚውል በመሆኑ ዋጋው አሻቅቦአል :: በዚህም የተነሳ እንደ ስንዴ የመሰሉ ሰብሎችን ያመርቱ የነበሩ መስኮችም ወደ በቆሎ ምርት በመዘዋወር ላይ ነበሩ :: ይህም በለጋሽ አገሮች ዘንድም የምግብ ውድነትን አምጥቶአል :: በነዚህ ላይ በዘይት ዋጋ መናር የተነሳ የትራንስፖርት ውድነት አለ :: በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ለጋሽ ሀገሮች እንደ አምስት አመት በፊቱ ረሃቡን ደብቀው ዕርዳታ ለማቅረብ የሚያስችል ሁኔተ ውስጥ ላይሆኑ እንደሚችሉ ከዚህ በፊት ጠቅሰን፣ መፍትሄውም ለዚህ ሃገራዊ ዕዳ ሃገራዊ አቅምን ማሰባሰብ ማነቆ የሆነውን የፖለቲካ ችግር መፍታት፣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አቅማቸው በዕውቀት፤ በገንዘብ፤ በጉልበት ወዘተ የሚረባረቡበት ሁኔታ እንዲመቻች አሳስበን ነበር ::

በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የፖለቲካና ገንዘብ ትርፍን ማስላት ከማንነቱ ጋር ያዋሃደው መለስ ዜናዊ ግን እኛ ያነሳናቸውን የአለም አቀፍ ለጋሾች ችግሮችን ግምት አስገብቶ ለርሱ በሚጠቅም መንገድ እርዳታውን ለመቆልመም እየታገለ ነው :: «እናንተ ጋ የእህል ውድነት ስላለ ፤ በዚህም ላይ የትራንስፖርት ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑም ከምዕራቡ እርዳታ መላክ በጣም ውድ ነው :: ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ጥሩ ምርት ያላቸው አካባቢዎች ብዙ በመሆናቸውና ፤የዕርዳታ እህል ከመጣ እነዚህ ከባቢዎች ምርታቸውን መሸጥ ስለማይችሉ ገበያዎቹ ይሞታሉ :: ገበሬውም ለሚቀጥለው አመት ለማረስ ፍላጎቱ ይቀንሳል :: በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የምግብ ዕርዳታ ከምትልኩ ከሃገሬው ገበያ እህሉን ገዝተን ለተቸገረው እንድናከፋፍል ብናደርግ እንመርጣለን :: መምረጥም ብቻ አይደለም ፤ ለመቀበል ዝግጁ የሆንነው ገንዘብ ብቻ ነው» እያለ በማስፈራራት ላይ ይገኛል::::

መለስ ለምን ገንዘብ እዕርዳታ ላይ ብቻ አተኮረ? ቀዳሚው ምክንያት ፤ በግንቦት 97 ምርጫ በህዝብ ይሁንታ ያጣውን የፖለቲካ ተቀባይነት፤ በ«ልማት መር» መንግስትነት አገኝዋለሁ ብሎ ራሱን በመሸንገል ፤ ህዝብ ያስቀመጣቸውን የክፉ ቀን ጥሪቶች ሁሉ አሟጥጦ በከተሞች ለሚከናወኑ የህንፃና መሰል ግንባታዎች እንዲውል አድርጎአል :: እነዚህ የ«ነጭ ዝሆን» ፋይዳ ቢስ ግንባታዎች ግን ለታይታ የሚደረጉ ካልሆነ በቀር ዘላቂ የሆነ የልማት አውታር ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልፅ ነበር :: እውነተኛውን የዋጋ ግሽበት ግምት ውስጥ በላስገባ ዝቅተኛ ወለድ ላይ የተጀመረው «የባንክ ብድር (ዝርፊያ) መር» ልማት ለመቀጠል እንዳይቻል ፤ የባንኩ ካዝና ተሰብሮአል :: የአቅጣጫ ለውጥ እንዳይደ ረግ ለመለስ ጉራ የማይመች ሆነ :: አማራጭ ሆኖ የተገኘው፤ በረሃብ የሚረግፈውን ህዝብ መያዣ አድርጎ፤ «የእህል ዕርዳታ አንቀበልም፤ በገንዘብ ካልሰጣችሁን ወዮላችሁ!» እያሉ የለጋሾችን ዐይን መደንቆል ነው ::

ሁለተኛውና ምናልባትም የበለጠው ምክንያት ግን፣ የማይጠረቃውን የወያኔ ካዝና መሙላት ነው:: ሁላችንም እንደምናስተውሰው «መትከል አግሪ ትከል ትግራይ» ወይም «ኤፈርት» በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ጥሪቱን ከየት እንዳመጣው መለስ ሲናገር «በትግሉ ዘመን ከለጋሾች ያሰባሰብነው ነው» ማለቱ ሃቅ ነው:: መለስ ያልተናገረው ነገር ግን እንዴት አድርገው እንዳሰባሰቡት ነው :: እኤአ በ1984/85 በነበረው ረሃብ ወቅት ፤ ወያኔ አሁን መለስ የሚከራከርበትን «ትርፍ ምርት ካለበት አከባቢ እየገዛን ለተራበው ህዝብ እናድላለን» በሚል «ፉድ ፐርቼዝ» መርሀ-ግብር ሽፋን፤ ከምዕራቡ የተቀበለውን ገንዘብ ሳውዲ አረቢያ ወደሚገኘው «የባንክ ኦፍ አሜሪከ» አካውንቱ በማዞር እንደሆነ፤ ምስጢሩን የሚያውቁ የወቅቱ ተጋዮች በየጊዜው አጋልጠዋል :: በትግራይ ህዝብ ረሃብ ስም ተለምኖ በወያኔ አከውንት ውስጥ የገባው የገንዘብ መጠንም በራሱ በመለስ አንደበት እንደተነገረው 100 ሚሊዮን ዶላር ነበር :: ከ20 አመተት በፊት ምዕራባውያን ያንን ያህል ገንዘብ ለአንድ ሽማቂ ድርጅት ሲሰጡ፤ ባልነበረው የዕርዳታ ማከፋፈያ አቅም ፤ በስሙ ለተለመነበት የትግራይ ህዝብ እንደማይውል ያውቁ ነበር ማለት ትክክል ይመስለናል :: የሶቭየት የጡት ልጅ የሆነውን የደርግ አገዛዝ ለመገርሰስ ይጠቅማል ብለው ስላመኑ «አይተው እንዳላዩ» ያደረጉት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ትብብር ነበር :: ዛሬስ? በኢትዮጵያ ረሃብተኛ ስም መለስ «የምግብ ዕርዳታ አልቀበልም የገንዘብ ካልሆነ» ሲል ለምን ዐይነት የፖለቲከ ዕርዳታ ሲሉ ሊተባበሩት አስበው ይሆን? ከአምስት(??) አመት በፊት ከለጋሾች የተቀበለውን የምግብ ዕርዳታ ለተረጂው ህዝብ ማድረስ የቻለው መንግስት፤ ዛሬ ይህን ማድረግ አቅቶት በርግጥም እንደተዘገበው 400 አስከሬኖች በቀን የምንቀብር ከሆነ፤ «ገንዘብ ካልሆነ የምግብ ዕርዳታ አልቀበልም» የሚለው የመለስ ስግብግብ ፖሊሲ «በሰው ልጅ ላይ የሚፈፀም የዕልቂት ወንጀል» አይደለምን? ከ20 አመታት በፊት በትግራይ፤ ዛሬ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የዕልቂት አዋጅ ያወጀብንን ጨካኝ እንዴት እንፋረደው ይሆን? በዝምታ ... በኪራላይሶን... በፓርላማ ትግል... ወይስ በመላ አቅማችን? ለግንቦት ሰባት መልሱ ግልፅ ነው:: ሁሉንም ዜጋ፣ ሁሉንም ጥበብ፣ ሁሉንም ጉልበት፣ ሁሉንም ሃብት በማሰባሰብ ሁሉን ዘዴ በመጠቀም በህዝብ እልቂት የሚያስነግድን ክፋትና ጭካኔን፣ መብት ረገጣንና ሃገራዊ ክህደትን ከሚፈለፈሉበት የገዛነብ መሃጸንም ቢሆን ገብተን መርታት ብቻ ነው::

## ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ፤ከገጽ1የዞረ

ነው።ሙስናን ከነሰንኩፉ ለመንቀል ከተፈለገ፤ዋነኛው መፈልፈያ ቋት የሆነው የመለስ አገዛዝ መወገድ አለበት “ብለዋል።በሌላ በኩል በችግረኛ ህዝብ ስም በብድር የተገዛ ንብረት በጂቡቲ ወደብ ተወርሶ መሸጡን የሰሙ የፖለቲካ ተንታኞች፤ “ታላቋና ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ - በትንሿ ጂቡቲ እግር ሥር የምትወድቅበት ጊዜ ደርሷል፤ለዚህም ዋነኞቹ የታሪክና የህግ ተጠያቂዎች 80 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚኖርባትን አገር ያለ ባህር በር ያስቀሩ የዘመኑ ገዥዎቿ ናቸው “ብለዋል።በቅርቡ የጂቡቲ መንግስት ፤የወደብ ታሪፍን 15 በመቶ ልጨምር ነው ብሎ ኢትዮጵያን በማስፈራራት፤ በፕሬዚዳንቱና በሴት ልጃቸው ስም ሰፋፊ ጋሻ መሬት መውሰዱ አይዘነጋም።

## አማረና- እሥራቱ ፤ከገጽ1የዞረ

ወደቀ።ከጦርነቱ በሁዋላ ጥቂት ራሱን የለወጠ የመሰለው ይህ ጋዜጣ ፤እንደገና ከግንቦት 97 ምርጫ ጋር ተያይዞ ኢህአዴግ ሲታመም እርሱም ማንከስ መጀመሩ በህዝብ አስተፍቶታል። ይህ ከኢህአዴግ መዋዠቅና መውሽልሽል ጋር አብሮ እየዋዠቀና እየተውሸለሸለ እዚህ የደረሰው የነባር ህወሀት አባሉ ጋዜጣ፤ ቅንጅት እንዲፈርስና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖረው ከፍተኛ ጥረት ያደርግ እንደነበር ታዛቢዎች ያስታውሳሉ። የቅንጅት አመራሮችና ጋዜጠኞች መታሰራቸውን አጥብቆ ይደግፍ የነበረው አማረ፣ነበር ።ጋዜጠኛም፣ አሳታሚም ነኝ የሚለው አማረ፤ ምንም ጥፋት ቢኖርባቸው እንኳ ፤ሁለት ደርዘን የሚሆኑ ጋዜጠኞች ለሁለት ዓመታት ያህል በታሠሩበት ጊዜ ለራሱ ሞራል ሲል አንድ ቀን እንኳ “ጋዜጠኞች ይፈቱ” ብሎ ለመፃፍ አልደፈረም ይላሉ። አማረ፤ የታገለለት ድርጅት አደጋ ውስጥ መውደቁን ሲያይ፣ ገለልተኛነቱን እንደ እራፊ ጨርቅ ወርውሮ፣ ህውሀትን ከውድቀት ለመታደግ ትልቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ታማኝነቱን ቢያስመሰክርም፣ ሰሞኑን የተፈጠረው ክስተት ግን ብዙዎችን የሚያነጋግር ሆኗል። አቶ አማረ በበረከት ስምኦን የሚመራውን የዳሽን ቢራ ፋብሪካን አሰራር ተችተሀል በሚል ሰሞኑን ጎንደር ውስጥ በእስር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የዋስትና መብት ቢሰጠውም እስከ ትናንት ድረስ አልፈታም እንዳለ ዘጋቢዎች ገልጸዋል። ስለጉዳዩ ያነጋገርናቸውና አቶ አማረን የሚያውቋቸው ሰዎች እንደሚሉት አቶ አማረ እጅግ ብልጥ፣ አድርባይና ስነምግባር የሚባል ነገር የሌለው ሰው ነው።እንዲሁም ራሱን እንደ መሪ የሚቆጥርና ለራሱ ያለው ትዕቢታዊ አመለካከት ለከት የለውም የሚሉት ውስጥ አዋቂዎች፤በቅርብ የሚያውቁት ተገናኝተው ስለ እርሱ ሲያወሩ ፦”ትንሹ መንግሥት፣ ራስ አማረ” እየተባባሉ እንደሚሳለቁበት ገልፀውልናል። አማረ ከግንቦቱ ምርጫ በሁዋላ የያዙት አቋምም መታየት ያለበት ከመተጣጠፍ ባህሪያቸው አንጻር ነው ያሉት እነዚህ አስተያየት ሰጭዎች፤ ከምርጫው በፊት የኢህአዴግ ተቺ መስሎ በመቅረብ ድጋፍ ለማግኘት ቢችልም፣ ከምርጫው በሁዋላ ግን ጥቅማቸው አደጋ ውስጥ መውደቁን ተረድተው ወደ አሳደገው ድርጅት መጠጋትን መምረጡን፤ ባህሪውን ያሳያል ይላሉ።

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ትንሽ ምክር ለመኮንኖች

ከመ/አ ደርሰህ ቸኮል(ዝዋይ)

“በአሁኑ ጊዜ በሲቪሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የተጠላው የህብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው?” ቢባል ያለምንም ጥርጥር መልሱ “ወታደሩና ፖሊሱ” የሚል እንደሚሆን አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ። በባድሜ ጦርነት ወቅት ወታደሩ የነበረው ህዝባዊ ተቀባይነትና ክብር ልዩ ነበር፣ለምሳሌ ለጦርነት ወደ ግንባር በሄድንበት ጊዜ የሚያውቀንም ሆነ የማያውቀን ኢትዮጵያዊ ሲመርቀን፣ አባቶች ባንዲራ አስይዘው ድል ይቅናችሁ ሲሉን፣ ለቤተሰቦቻችን ድጋፍ ሲደረግ፣ ከአራቱም ማእዘናት ሰንጋ ሲጫንልን፣ ከውጭ አገር ሳይቀር ስጦታው በአይነት በአይነት ሲቀርብልን ወዘተ ተመልክተን ወታደር በመሆናችን ምን ያክል እንኮራ እንደነበር በጊዜው የነበርን ሁሉ የምንረሳው አይመስለኝም። ከወንድሜ በፊት እኔ ልቅደም እየተባባልን ፈንጅ ወረዳ ውስጥ ዘለን የገባነው፣ ለምሽግ ሰበራ እየተሽቀዳደምን በጠላት መሳሪያ የሞትነውና የቆሰልነው ህዝባዊ ድጋፉ ፈንቅሎንና ህዝባዊ አደራው ከብዶብን እንደነበር ብናገር ዋሾ የሚለኝ እንደማይበዛ አምናለሁ። ይሁን እንጅ ያ ከድል በፊት የነበረን ክብርና ተቀባይነት ከድል በሁዋላ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ አልቻለም።ህወሐት እንደተከፋፈለች የአንጃው ደጋፊ እየተባሉ ብዙ ጀግና ወታደሮች ተገደሉ፣ታሰሩ ወይም ተባረሩ። በሰራዊቱ ውስጥ ፈጽሞ የማይታወቁና ምንም ጀብድ ያልሰሩ ካድሬዎች የፖለቲካ ታማኝነታቸው እየታየ ወደ አመራር ቦታ ብቅ አሉ።ህዝባዊ ሰራዊት የሚለው ቅጽል የመለስ ሰራዊት በሚል ቅጽል እየተተካ መጣ።

በጦርነቱ ማግስት ሰራዊቱ ድንበሩን በተመለከተ ስለሚኖረው ግንኙነት ምንም ነገር እንዳይተነፍስ በመደረጉና ባድመም ለኤርትራ መወሰኑ እንደተሰማ ምንም ተቃውሞ ለማሰማት ባለመቻሉ ህዝቡ ሰራዊቱን እንዲንቅና አመኔታ እንዲያጣበት ተጨማሪ ምክንያት ሆነ። የኤርትራ ጉዳይ ሳያልቅ ደግሞ የግንቦቱ ምርጫ መጣ። የእነ መለስ ቡድን ወታደሩ መንግስትን ደግፎ እንዲቆም ውትወታ ያደርጉበት ጀመር። ውትወታቸውን አልቀበልም ያለውን ወታደር ነፍጠኛ ና ኦነግ እያሉ በግምገማ ማዋከብ ቀጠሉ። ፖለቲካ ውስጥ አታስገቡን እያሉ በድፍረት የተናገሩ ቆፍጣና ወታደሮች ታሰሩ፣ ተደበደቡ፤የቅንጅት ደጋፊዎች እየተባሉም ብዙ ግፍና መከራ ደረሰባቸው። የተወሰኑ ሆዳም ወታደሮች ደግሞ ለመለስ መንግስት ታማኝነታቸውን ለመግለጽ በሰኔ አንድና በጥቅምት ሀያ ሁለት ለዲሞክራሲና ለነጻነት ጥያቄ በተነሱ ወንድሞች፣እህቶች፣ እናቶችና አባቶች ላይ ቃታቸውን ሳቡ። በእርግጥም ተቃውሞ ለማንሳት አስበን እንደነበር ቢደርሱብን ኑሮ ዛሬ ይህን ጽሁፍ የምጽፍላችሁ ሰማይ ቤት ውስጥ ሆኜ ይሆን እንደነበር አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ።

የግንቦቱ ምርጫ በህዝቡና በወታደሩ መካከል ብቻ ሳይሆን በወታደሩና በመኮንኖች፣ በወታደሩና በወታደሩ እንዲሁም በወታደሩና በካድሬው መካከል መተማመን እንዳይኖር አደረገ።በህዝቡ የተነሳውን ተቃውሞ ለማፈን ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ወታደሮችና መኮንኖች ከማእረግ እድገት አንስቶ እስከ ገንዘብና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ድረስ ተሰጣቸው። በአንጻሩ ንጹሀን ዜጎችን መግደል፣ሊያሳፍር እንጅ ሊያሸልም አይገባም ብለው፣እራሳቸውን ከድርጊቱ ያገለሉ ወታደሮች ዛሬ ድረስ ታማኝነታችሁን ግለጹ እየተባሉ ይዋከባሉ።

ጓደኞቻችን በህዝቡ ላይ የፈጸሙትን ወራዳ ተግባር ተከትሎ ፣ህዝቡ አይናችሁን ላፈር አለን። እንደ ድሮው ሰላም የሚለን፣እንደ ድሮው ቀርቦ የሚያናግረን ጠፋ።ቤተሰቦቻችን ሳይቀር ድሮ የነበራቸውን አክብሮት ቀንሰው ቶሎ ከሰራዊቱ የምንገለልበትን ሁኔታ እንድናመቻች ይወተውቱን ጀምረዋል።

ከዚህ አጣብቂኝ ሳንወጣ ደግሞ በእንቅርት ላይ እንዲሉ የሶማሊያ ጦርነት መጣ። ጦርነቱን ለመጀመር ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ጦርነት ሲመጣ ልዩነቱን ወደጎን ይተውና አንድ ይሆናል የሚል እምነት በስፋት ነበር። ወታደሩ በሰኔ አንድና በጥቅምቱ 22 ለሰራው ስህተት ከህዝብ ይቅርታ የሚያገኝበት ጥሩ አጋጣሚ እንደተፈጠረለት ስላሰበ ተደሰተ።ይሁን እንጅ ያ የታሰበው ድጋፍ አልተገኘም፣ ይባስ ብሎ፣ ህዝቡ “ሶማሌ ከዳር እና ከመሀል” እያለ ለልጆቹ ሞትን ተመኘ።ይህ ለእኛ የሞት ሞት ነበር። ለማንና ለምን እንደምንዋጋ ግራ ገባን።

መንግስትም በእልህ ጦርነት ውስጥ ገባ። መውጫህን ሳታይ አትግባ የሚባለውን የአበው ምክር ወደ ጎን በመተው ዘው ብሎ ገባና አሁን መውጫ ቀዳዳ ጠፍቶበት እየተንደፋደፈ ይገኛል። ለመቁጠር የሚያታክት ወንድሞቻችን በእየቀኑ ያልቃሉ። ለሚሞቱት ወታደሮች የኢትዮጵያ ህዝብም አያዝንላቸውም፣ እንዲያውም “እንኳን ሞቱ፣ ምነው በጨረሳቸው እያለ” ነው። “ሶማሌን ነጻ ልናወጣህ ነው የመጣነው”ስንለው “መጀመሪያ እራስክን ነጻ አውጣ” ብሎ ይመልስልናል ።እንግዲህ ወይ የሶማሌ ወይ የኢትዮጵያ ህዝብ ካልወደደንና ካልደገፈን ለማን ነው የምንዋጋውና የምንሞተው? ሁለቱም ሞታችንን ሲመኙልን እኛ ለምንድነው ለእነሱ ለመሞት የምንቸኩለው?

የሶማሊያ ሳያንስ እንደገና ደግሞ የሱዳን የድንበር ጥያቄ መጣ።የእኛ ስራ ከድንበር ጥበቃ ወደ ቤተመንግስት ጥበቃ ተሸጋግሯል።

ወንድምና እህት መኮንኖች፣ መንግስት አገራችንን ከጥፋት ወደ ጥፋት ሲወስዳት እየተመለከትን አንድም ቀን አንደበታችንን ከፍ አድርገን ለመቃወም የቻልንበት አጋጣሚ የለም። ሁሌም መንግስት እንደፈለገ ሲያስሽከረክረን፣በጥቅማጥቅም ሲደልለን የራሳችንን ጥቅም እያስቀደምን የአገራችንን ጥቅም ወደ ጎን እየገፋን ስንመጣ ቆይተናል። ምናልባትም በጥቅምት ከኤርትራ ጋር ጦርነት ይጠብቀን ይሆናል። የሶማሊያን መውጫ አጥተን በሌላ ግንባር ጦርነት ቢከፈትብን ወይም ብንከፍት አሁን ባለው የመነመነ ህዝባዊ ድግፍ ድል እንደማናደርግ እርግጥ ነው። በዚያ ላይ የኑሮ ውድነቱና ረሃቡ አለ።ችግሩን ብቻ ማውራቱ ፋይዳ የለውም። መፍትሄ ፍለጋው ላይ መረባረብ አለብን። ለመፍትሄው ደግሞ ከእኛ የተሻለ ቅርበት ያለው አካል ያለ አይመስለኝም። እኛ በሰራዊቱና በአገራችን ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ ከፈለግን በመጀመሪያ እራሳችንን በማጎብደድ ከምናገኘው ጥቅማጥቅም ማራቅ አለብን። በመንግስት ላይ እንዳንነሳና ባሪያ ሆነን እንድንገዛ ያደረገን ይህ ነው። አገራችን ችግር ውስጥ ስትገባ፣ ህዝቡ በረሀብ ሲያልቅ እያየን፣እኛ በተሻለ ኑሮ ውስጥ ስላለን ብቻ እንዳላየን በዝምታ የምናልፈው ከምቾታችን የምንፈናቀል ስለሚመስለን ነው። መንግሰትም ይህን ስለሚያውቅ ሁሌ በጥቅማጥቅም ሊደልለን ይሞክራል። አንዳንዶቻችሁ ከሰራዊቱ ጥሎ መውጣትን እንዳመራጭ እያያችሁት ባገናችሁት አጋጣሚ ሁሉ ትንሽ ሀብት ይዛችሁ ለመውጣት እንደምትሞክሩ አውቃለሁ።ይህ ግን ጥሩ መፍትሄ አይመስለኝም። ለጊዜው እረፍት ታገኙ ይሆናል ነገር ግን ተመልሳችሁ እዛ ህዝብ መሀል ስለምትገቡ ሰላማችሁ መልሶ ይደፈርሳል።ከሰራዊቱ ጥለን ከምንወጣና የሲቪል ኑሮ ለመኖር ከምንናፍቅ ይልቅ፣ በሰራዊቱ ውስጥ ሆነን ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ ብንፈልግ የተሻለ ነው ብየ አምናለሁ።

ብዙ የለውጥ ሀይል የምትሆኑ ወጣት መኮንኖች እንዳላችሁ አውቃለሁ። ለጥቅም የማትገዙ መኮንኖች እንዳላችሁም አውቃለሁ። ነገር ግን እናንተ ላገር ኩራት የምትሆኑት እራሳችሁን በስውር አደራጅታችሁ ለለውጥ መነሳት ስትችሉ ብቻ ነው። በእኔ እምነት በመፈረካከስ ላይ ያለችውን ኢትዮጵያን ለማዳን ሁነኛ መፍትሄ ያለው በእናንተ እጅ ነው። እግዚአብሄር የለውጥ ሀዋርያት ያድርጋችሁ፣ያድርገን።

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## በጥባጭ ካለ፤ ጥሩ አይጠጣም

ጋቹዬ

1–በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የረዥም ዓመታት የህፃናት ፕሮግራም አዘጋጅ የሆኑት አባባ ተስፋዬ በ1998 ዓ.ም መስከረም ወር ባስተላለፉት የአዲስ ዓመት መግቢያ ልዩ ዝግጅታቸው ላይ ፦" አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የአንድነትና የእርቅ ይሁንልን "ብለው በመመረቃቸው ከደመወዛቸው ላይ የገንዘብ ቅጣትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ እንደተወሰደባቸው በጊዜው በተለያዩ ፕሬሶች መዘገቡን ይህ ፀሀፊ ያስታውሳል።እንደ ፕሬሶቹ ዘገባ፤ አባባ ተስፋዬ ለመቀጣታቸው የተነገራቸው ምክንያት፦"ማንን የተጣላ ዐይተሀል እርቅ እርቅ የምትለው?"የሚል ነው።

2–ይህ ከመሆኑ ከአንድ ወር በፊት ቅንጅት ላቀረበውና ወደ ብሄራዊ መግባባት ለሚወስደው "የብሔራዊ አንድነት መንግስት ምስረታ "ጥያቄ፤ኢህአዴግ የሰጠው መልስ ፤ "ጥያቄው ህገ-መንግስታዊውን ሥርዓት በህገ-ወጥ መንገድ ለመናድ የታሰበ ወንጀል ነው" የሚል ነበር።(ልብ በሉ፣ ይህ ምላሽ የተሰጠው፤ ምርጫ 97ትን ተከትሎ አገሪቱ ከፍተኛ ውጥረት በገባችበት ጊዜ ለቀረበ የመቻቻል ጥያቄ ነው)

3–አቶ መለስም ሆነ ግልገል ሹመኞቹ በተደጋጋሚ ሲናገሩ እንደተደመጡት፣እንዲሁም በተለያዩ የድርጅታቸው መመሪያና ፖሊሲዎች ላይ ሳይቀር እንደሰፈረው፤ የብሔራዊ እርቅ ጥያቄ - "የፀረ-ሰላም ሀይሎች አጀንዳ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል - በገዥዎቻችን ጎራ።ሌላም ሌላም...

ይህን ነገር ዛሬ ለማስታወስ የተገደድኩት፤ አንዳንድ ወገኖቻችን ስለ እርቅና መስማማት አስፈላጊነት በመጥቀስ ፤ በአሁኑ ጊዜ ጨርሶ በአገራችን እየጠፋ ላለው የመቻቻል ፖለቲካ በደምሳሳው ሁሉንም የፖለቲካ ሀይሎች እኩል ለመውቀስ ሲቃጡ በመታዘቤ ነው።አውቀውም ይሁን ባለማወቅ ይህ በእውነተኛ ምክንያታዊ ትንታኔ ያልታገዘ ድምዳሚያቸው፤ ህሊናቸውን ለሚያከብሩ ዜጎች የሚዋጥ አይደለም። በአሁኑ ወቅት ለእርቅና ለመቻቻል ሳንካ የሆነው ብቻ ሳይሆን በተፃራሪው ጥልን በማስፋፋት አገሪቱን ወደ ጨለማ እየወሰዳት ያለው ዋነኛው ሀይል ፤የገዥው ቡድን መሆኑን ላለመገንዘብ አውቆ የደነቆረ ወይም ፈርቶና ለጥቅም ብሎ ከህሊናው የሸሸ ካለ፤ አለቃው መለስ እንደሚው፦"መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት"

አዎ! አገራችን ኢትዮጵያ ለተዘፈቀችበት ሁለንተናዊ ቀውስ ፤ ዋነኛውና መሰረታዊው መፍትሔ የኛ የልጆቿ መታረቅ፣ መስማማትና መግባባት መሆኑን ጤናማ የሆነ ሁሉ የሚያምንበት ሀቅ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ አገራችንን አስመልክቶ በመካከላችን የቆመው የልዩነት ግንብ እንዲፈርስ ከተፈለገ፤ የዘመኑ ሰናዖራውያን (የጥላቻ ግንበኞች)፤ በማያሻማና በማያንገራግር ቋንቋ ገለል ሊሉ ይገባል የሚል ፅኑ እምነት እስከመሰነቅም ደርሰናል።

"ስለመታረቅና ስለመስማማት መፍትሄነት እየተናገርክ፤ እንዴት ገዥዎቻችን መገለል አለባቸው ትላለህ?" የሚል ካለ፤ ለመቻቻል ስርዓት ዋነኛ ጋሬጣዎች፣ ለብሔራዊ እርቅ ዋነኛ እንቅፋቶች፣ ለይቅርታ መንፈስ ዋነኛ ጠላቶች፣ ለፍቅር ኑሮ ዋነኛ ፀሮች ስለሆኑ ነው። አበው፦"ባለጌን የወለደ አነቀ፤ፀደቀ" እንዲሉ፤የመቻቻል ባህል ባለው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ጥልንና ቂምን የዘሩና እየዘሩ ያሉ የክፋት ቋቶች እነሱ በመሆናቸው ነው መነቀል አለባቸው የምንለው- አንድነትና እርቅ ሲባል የሚበረግጉ የጥላቻ ደቀ-መዝሙሮች እነሱ ስለሆኑ ነው በቃችሁ መባል አለባቸው የምንለው። አዎ!ዋነኞቹ ጥል በታኞች ገበታውን ሰፍረውበት ሌሎቻችን እንዴት በሌማቱ ዙሪያ በሰላም እንቀመጥ?

**በጥባጭ ካለ እንዴት በሰላም ይጠጣል?**

በመግቢያዩ ላይ የጠቀስኳቸውን የአጭር ጊዜ ትዝታዎቻችንን ትንሽ ፈታ አድርገን ብናያቸው ፤በኢህአዴግና- በእርቅ ( በአንድነት )መካከል ያለውን የማይታረቅ ቅራኔ በመጠኑ ሳያሳየን አይቀርም ።ምርጫ 97ትን ተከትሎ በተከሰተው የህዝብና-የገዥዎቻችን ፍጥጫ አገሪቷ ወደ ችግር እየገባች መሆኗን አባባ ተስፋዮ ሲያዩ፤ አባ ጳውሎስ በቃለ-ምዕዳናቸውና ሼህ ኤሊያስ በዝየራቸው ሊያነሱት ያልደፈሩትን የእርቅና የአንድነት ጉዳይ፤ በልጆች ፕሮግራማቸው ዝግጅት ፍፃሜ ላይ ተናገሩ። የፍቅር አባት ናቸውና ልክ ቴዲ አፍሮ ገዥዎቻችንን፤ እንደ ሰው አምኖና እንደ ሰው የፍቅር ልብ ያላቸው መስሎት፦

**" ሆ! በል ዋሽንቱ ሆ! በል ማሲንቆ፣**

**ስታይ ሰው ታርቆ** " ብሎ በአበባየሆሽ ዘፈኑ እንዳለው ማለት ነው። እናም አባባ ተስፋዬ እርቅ በማለታቸው "ማንን የተጣላ አይተሀል እርቅ የምትለው?"ተብለው ተቀጡ። እርሳቸውም እንደ ቴዲ በመኪና ገጪ። ሆኖም ያደረሱት አደጋ ቀለለ መሰል ቅጣቱ በብር አለፈ። በጊዜው በሁኔታው የተገረሙ አስተያየት ሰጭዎች፦"አባባ ተስፋዬ አዲሱ ዓመት የብጥብጥ፣የጥላቻና የመበታተን ዓመት ይሁንልን!" ቢሉ ይሸለሙ ነበር ወይ? ብለው እስከመጠየቅ ደርሰው ነበር።ከዚያም ባሻገር "ይህ አጀንዳ የቅንጅት ነው" የሚለው አቋም በገዥዎቻችን ተደጋግሞ መስተጋባቱ ግራ የገባቸው ፕሬሶች፦"እርቅን፣ፍቅርን፣መቻቻልንና ሰላምን ለቅንጅት ብቻ ማን ሰጠው? ኢህአዴግ ሆይ! እነዚህ ነገሮች የአንተም፣የቅንጅትም፣ የሌሎችም፣የሁላችንም በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ናቸው" ብለው ደጋግመው ፃፉ-በጊዜው።በአመዛኙ በየሳምንቱ በየርዕሰ-አንቀፆቻቸው የሚያስተጋቡት አቋም፦"ብሔራዊ እርቅ"የሚል ነበር። በአፀፋው ከገዥዎቻችን ያገኙት ምላሽ ማዕከላዊ ጨለማ ቤት መታጎርና ከርቼሌ መወርወር ሆነ። ዐቃቤ ህግ በጋዜጠኞች ላይ ለመሰረተው ክስ ያቀረበው ማስረጃ በሙሉ የየጋዜጦችን ርዕሰ-አንቀፅ ነበር።አስገራሚው ነገር፤ በሌላው ዓለምም ሆነ ፤አሁን ጨካኙ ህግ ከመፅደቁ በፊትም በጊዜው በአገሪቱ በነበረው በአፋኙ የፕሬስ ህግ ሳይቀር፤ በርዕሰ-አንቀፅ ሃሳብን መግለፅ የማያስጠይቅ ሆኖ ሳለ መከሰሳቸው ብቻ አይደለም-ከርዕሰ-አንቀፆቹ የጋዜጠኞቹን ክስ ያጠናክራሉ ተብለው የተመረጡትና በነ ቁጭ በሉ ፍርድ ቤት ከተነበቡት አብዛኞቹ፦" የብሔራዊ አንድነት መንግስት ይቋቋም! " የሚሉት መሆናቸው እንጂ። ዓቃቤ ህግ ለእነዚህ ርዕሰ-አንቀፆች ያስመዘገበው ማጠናከሪያ ጭብጥም፦"የቅንጅትን የብሔራዊ አንድነት መንግስት አጀንዳ የራሳቸው አድርገው በመውሰድ ህገ-መንግስታዊውን ስርዓት ለመለወጥ በፅሁፍ ተሳትፈዋል" የሚል ነው።

ታዲያ..ታዲያ... እርቅና መቻቻል በሚያስፈልጋት አገር፤ስለ እርቅና ስለ አንድነት መዝፈን፣መናገርና መፃፍ በከባድ ወንጀል የሚያስከስስና የሚያስቀጣ ከሆነ፤ያለ ጥርጥር ፍቅርን እየገፋ ያለውን አካል ማስወገድ ቅድሚያ የሚከወን ተግባር ሊሆን ግድ ይገባል ስንል የሚከራከር ማነው? "ኢትዮጵያ የኔና የቡድኔ ብቻ ናት" ከሚል የስልጣን ጥማት በመነሳት በህዝቦች መካከል የጥላቻ ቤንዚን እያርከፈከፈ ያለውና ፍቅርን አሻፈረኝ ብሎ የረገጠው አገዛዝ በተባበረ የህዝብ ክንድ ሊደቆስ ይገባል ስንል ቅር የሚለው ማነው? መፅሀፉስ ቢሆን ፦" **የእግዚአብሔር ነፍስ ትፀየፈዋለች" አይደል የሚለው?** ማንን? **በወንድማማቾች መካከል ፀብ የሚዘራውን**!ስለዚህ የነፃነትን፣የሰላምን፣ የእርቅንና የመቻቻልን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የናፈቅክ ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ለድህነት፣ለረሀብ፣ለጉስቁልና፣ለውርደትና ለሞት እየዳረገን ያለው፤ የኢትዮጵያን ህዝቦች በአንድ የፍቅር ገበታ ዙሪያ መቀመጥ አጥብቆ የሚጠላው በታኙ የነመለስ የጥላቻና የክፋት ቡድን መሆኑን ያለአንዳች ማቅማማት በመገንዘብ፤ ይህን የጥላቻ ሀይል በተባበረና በተሳሰረ የህዝብ ሀይል ለማስወገድ ለሚቀርብልህ ራስንና አገርን የማዳን ትግል ጥሪ፣ምንጊዜም በተጠንቀቅ ሆነህ ትቆም ዘንድ እንጠይቅሀለን።

**በጥባጭ ካለ፤ ማን ጥሩ ይጠጣል?**